

<u>ነፍስ፡ይማር።</u>

ድሮም፡መንናኝ፡ነበር፡ዛሬ፡ግን፡አርረገ፣
ከፈጣሪው፡ጋራ፡ኑሮውን፡አረገ።
ፍልስፍና፡ታሪክ፡የነበር፡ተጠሪ፣
ቅን፡ተመራማሪ፡ሀገር፡ሕዝብ፡አፍቃሪ፣
ጣሻና፡ዋሻውን፡መረጃ፡ቆፋሪ፣
ከኑቢያ፡ገዳም፡ብራና፡አስክርባሪ፣
የኢትዮጵያን፡ታሪክ፡ለወገን፡አብሳሪ።
ፈረንጅ፡አምላኪዎች፡ጨቅጭቀው፣ነዝንዘው፣
ያው፡ትቷቸው፡ሄደ፡እንደ፡ልብብ፡ይስፋቸው፣
ሥራው፡ሞግቷቸው፡ሊያስተካክላቸው፣
በንጹሕ፡ኅሊናው፡እየመከራቸው፣
ሀገርና፡ወገን፡ሊሆን፡ትኩረታቸው።
ኢትዮጵያ፡አገራችን፡እግዚአብሔር፡ያጥናሽ፣
መሪራስ፡ልጅሽን፡እንዲህ፡ስላጣሽ።

ልብብ፡ያልለው፡ልብብ፡ይበል፣ኀዘን፡በዝቶብሻል፣
ሊቃውንት፡ልጆችሽ፡በብዛት፡አልቀውል፣
ስለዚህ፡መሪራስ፡ዓማን፡በላይ፡አልፏል፣
ነፍሱን፡ይማርልን፡በገነት፡ቤት፡ትዋል።

ለቤት፡ሰዎች፡እና፡ዘመድ፡አዝማድ፡ወገን፡መጽናናትን፡ያውርድልን።አሜን።

ጽሑፎቹን፡በመጠኑ፡ካነበቡት፡አንዱ፣

ስለሺነህ፡ገላነህ፣
ካናዳ።